# የእግዚአብሔር ፍቅር

“…እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” ኢሳ 48፥17

God's Love, P.O.Box 6734, L.S. MO 64064.
E-mail mtizazu@hotmail.com -Fax/Ph 816-246-9395

ግንቦት 1994 MAY 2002

“ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ።” ኢሳ 54 ፥ 13

## *ከፀሎት መልስ ጋር መተላለፍ*

በአንድ ሐገር የሚኖር አንድ ገበሬ ለጉዳይ ሐገር አቋርጦ በእግሩ ይጓዝ ነበር። የሚጓዘውም ተራራማ ሸለቆአማ በሆነ ጫካ አቋርጦ ነበር። ከማለዳ ጀምሮ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ድረስ ከተጓዘ በኋላ ድካም ይፈታተነው ጀመረ። ሆኖም የባላገር ነገር የትም ጎራ ብሎ አይታደርምና እስከሚቀጥለው መንደር ድረስ ተግቶ መገስገስ ነበረበት።

መንገደኛው ገበሬ በመጠንከር በዚያ በክረምቱ ዝናብ በጨቀየው ስምጥ ሸለቆ አፋፍ ለማለፍ ተጨማሪ ጥንቃቄ በማድረግ ጉዞውን ቀጠለ። የሸለቆውንም አፋፍ ለማለፍ ትንሽ ሲቀረው ፥ በድንገት ጭቃው አዳለጠው። ፋታም ሳይሰጠው አንሸራትቶ ወደ ገደሉ ወረወረው። ከዚያ በኋላ ራሱን ያገኘው በደመነፍስ ጨብጦ በተንጠለጠለበት በአንድ ቅርንጫፍ ላይ ነበር። ከዚያም በድንጋጤ ቁና ተነፈሰና አካባቢውን አስተዋለ። አስፈሪ ሁኔታ ነበር። ወደ ላይ ሊያወጣው የሚችል ተዓምር ብቻ ነው። ወደ ታች ወደ ሸለቆው ቢወድቅ ግን ያው ሞት ነው የሚጠብቀው።

መቼም ተስፋ ሁሉ ሲሟጠጥ ወደ እግዚአብሔር መመልከት የሰው ባሕሪይ ነውና፥ቀና ብሎ ወደ ጌታ መፀለይ ጀመረ። “ወየው ጌታዬ ሆይ! ፈጥነህ ካልደረስህ መሞቴ ነውና ቶሎ ድረስልኝ” “አምላኬ አምላኬ” እያለ በስቃይ ቃተተ።

ምንም ያህል ሳይዘገይ ፥ ጌታ በሰው ተመስሎ ተገለጠና :- አንተ ሰው ተርፈሃል? ሲል ጠየቀው። ሰውየውም ጌታ መሆኑን ሳያስተውል፡ “አውጣኝ ፥ ቶሎ ብለህ አንድ ነገር አድርግ” “ሐረግ ፈልግ” “ገመድ ፈልግ” እያለ ይጮህ ጀመር። ጌታም የመጣው ሊያድነው ነውና፥ በል፡ ላወጣህ ነኝና ፡ የተንጠለጠለህበትን (የያዝኸውን) ቅርንጫፍ ልቀቅ አለው። ሰውየውም “ምን ዓይነት ንግግር ነው? ” ብሎ ተገረመ። “የተንጠለጠልሁበትን ይህንን ቅርንጫፍ ከለቀቅሁማ ወደ ገደሉ ወድቄ መሞቴ ነው።” “ታድያ ምኑን ረዳኸኝ?” “እባክህ ሌላ የሚጥም መላ ፈልገህ አድነኝ።” እያለ ከጌታ ጋር ክርክሩን ቀጠለ። ጌታም ብዙ ካባበለው በኋላ በሰውየው አለማመን አዝኖ፥ተለየውና ሄደ።

በዚህ አኳኋን ለትንሽ ጊዜ ተንጠልጥሎ ከቆየ በኋላ የክንዱ ጡንቻ እየከዳው ሄደ። የመጨረሻዋ የጉልበቱ ጠብታ ስትሟጠጥ በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ ሸለቆው ጥልቀት ወደቀ። ምንም አልቀረውም። ቀድሞውንም አጅግ ተዳክሞ ስለነበረ ፥ ነፍሱ ልትወጣ ብዙ አልቆየችም። ምድራዊ ዘመኑ በዚሁ አበቃ።

መቼም ሰውየው አማኝና የፀሎት ሰው ነበረና ልክ ነፍሱ ከዚህ ስተወጣ ፡ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ነቅቶ ራሱን አገኘ። ከዚህ ዓለም መከራ በመገላገሉ በተሰማው ሰማያዊ ሐሴት በረዥሙ ተነፈሰና አረፍ ካለ በኋላ:- ጌታን አንድ በጣም ግራ የገባውን ነገር ሊጠይቅ ፈለገ። ጌታም ምንድን ነው ልትጠይቀኝ የምትፈልገው? ሲል ለጥያቄው መንገድ ከፈተለት። ሰውየውም :- “ሞቼ ወደ እዚህ ከመምጣቴ በፊት በሞት አፋፍ ሆኜ ፥ እንደዚያ ተጨንቄ ስፀልይ ያልደረስህልኝ ለምን ነው?” ሲል ጌታን ጠየቀው። ጌታም:- ልጄ የማታስተውለው ለምን ነው? በጠራኸኝ ጊዜ ወዲያው መጥቼ አልነበረምን? የያዝኸውንም ለቅቀህ እጅህን ስጠኝ! ያልሁህ እኔ አይደለሁምን? አንተም የያዝኸውን የሙጥኝ ይዘህ እስከ ሞት አልተንጠለጠልህበትምን? ለፀሎትህ መልስ ሳልሰጥ ቀርቼ ሳይሆን፥ ባለማመን ስላልተቀበልኸው ነው፤ ሲል ጌታ መለሰለት። ወዲያውም ነገሩ ትዝ አለው። ሁለተኛም ሊጠይቅ አልቃጣውም።

አንተስ፥ የምትፀልየው ስለ ምንድን ነው? ስትፀልይ የፀሎትህን መልስ ትቀበላለህ? በቅርቡ የተመለሰ ፀሎት አለህ? ወይስ ተዓምራት ታሪክ ብቻ ሆኖብሃል? ከፀሎትህ መልስ ጋር ተላልፈህ ይሆን? ከሆነስ ለምን ይሆን?

መጽሐፍ እንዲህ ይላል :- “ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፡የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።” (የያዕቆብ መልዕክት 1፥ 6-8)
“… አምናችሁ በፀሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ …” (የማቴዎስ ወንጌል 21፥22)

ሰው በሚፀልይበት ጊዜ ፀሎቱ በምንም አኳኋን ቢመለስ ለመቀበል ራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል። በተጨማሪም ሁሉን አዋቂ የሆነው ጌታ ለልጆቹ የተሻለውን እንጂ ያነሰውን እንደማይሰጥ ማመን ያሻል። የእርሱ ስጦታ አይሳሳትም። ሰው ለራሱ የሚመኘው ግን የሚያጠፋው ወይም የሚያባክነው ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ስለዚህ በየቀኑ አጋጣሚዎች የጌታ መልስ ሊመጣ ስለሚችል በማስተዋል ነቅቶ መጠባበቅ ያስፈልጋል። ለሚያስተውል የእግዚአብሔር ባሪያ ቀኖች ሁሉ በተዓምራት የተሞሉ ናቸው። አንተም ከዛሬ ጀምሮ ለረዥም ጊዜ ስትፀልይበት የኖርኸውን ልመናህን ለመቀበል ተዘጋጅ! የሚያጋጥሙህን ሁኔታዎች ሁሉ በማስተዋል ተመልከት። ፈውስህና በረከትህ በደጅ ነው። በእጅህ የያዝኸውን፥ የተንጠለጠልህበትን ነገር፥ ልቀቅና በእግዚአብሔር እጅ ላይ ውደቅ። ከእጆቹ አምልጦ የወደቀ፥የተጎዳም ተሰምቶ አይታወቅምና። ጌታ ይመስገን።

******************

## “ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና” (1ቆሮንቶስ 5፥7)

ፋሲካ ከባርነትና ከሞት የማምለጥ ጉዳይ ነው። የጌታ ፍርዱ በተነሣበት ወቅት ከሚፈጠረው ሞት ወዳጆቹን የሚሰውርበት አሠራር ነው። ይህ በእስራኤል የተጀመረው ሥርዓት የተሻረ ሳይሆን የታደሰ ሥርዓት ነው። የአዲሱ ኪዳን ፋሲካ ከቀድሞው የበጎች ኮርማ ከፍ ወዳለው፥ከሰው ወደ ተወለደው፥ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ መታረድ ከፍ አለ። እንዲህ ነው:- “እግዚአብሔር በግብጽ ሐገር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው:- … በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት፥…ይውሰድ። …እያን

ዳንዱም እንደሚበላው መጠን ከጠቦቱ ይካፈሉ:: የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት ... ይሁን፤ ... የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት:: ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቀቡት:: ... እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው:: እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ ሐገር አልፋለሁ÷በግብፅም ሐገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኩርን ሁሉ እገድላለሁ፥በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ፥እኔ እግዚአብሔር ነኝ:: ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙን ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ ፤ እኔም የግብፅን ሐገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም::" (ኦሪት ዘጸአት 12÷1-13)

ውድ ወገኖቼ፡- በዓለም ላይ የሚመጣው ፍርድ በግብፅ ላይ ከሆነው ፍርድ ይከፋል:: የማይዋሸውና ፡ የማይሻረው የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ስሙ፡-"እነሆ÷እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል ፤ ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ ፤ የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል ÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች÷..." (ትንቢተ ሚልክያስ 4÷1-2)

የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ÷ በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመቃንህና በጉበንህ አለ? የተሰቀለው÷በመታረዱም ምክንያት ሰውን ሁሉ ለማዳን የተቻለው ኢየሱስ ምንህ ነው? ጥያቄዬ ኃይማኖትህ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ አይደለም:: ኃይማኖተኛነት አያድንም:: ኢየሱስንም የሰቀሉት ኃይማኖተኞች ናቸው:: ነገር ግን የሞት መልዓክ ዛሬ ቢመጣ ወደ ቤትህ እንዳይገባ የሚከላከል አለህ? አስተውል:: የፍርድ ቀን ሩቅ አይደለም:: የማይታዘዙት ይፈረድባቸዋል:: የታረደውን ÷ እግዚአብሔርም ከሞት ያነሣውን ኢየሱስን "ለተቀበሉት ሁሉ ግን ÷ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" (የዮሐንስ ወንጌል 1÷12) "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

**የንስሐ ፀሎት፡-** እግዚአብሔር ሆይ÷ስለ ሰዎች ኃጢአት ተፈርዶበት በቀራንዮ መስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ለእኔ እንደ ሞተ አምናለሁ:: ከዛሬ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱሴን በማንበብና ወንጌል የሚሰበክበት ቦታ በመገኘት የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅና ለመከተል እተጋለሁ:: ያለፈውን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ:: በመንግሥትህም ተቀበለኝ:: ስለ ስምህ::አሜን::

---

ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ፀሎት የፀለይህ ከሆነና የምታነበው መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለህ÷ በነፃ ወይም በዋጋ እንድንልክልህ÷በአድራሻችን ከአጭር ምስክርነት (መግለጫ) ጋር ጻፍልን::

ኢየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::

መላኩ ትዕዛዙ

---

አድራሻችን፡- God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit, MO 64064 ነው::

---

ውድ ወገኖች ፡- ደብዳቤአችንን እንዳነበባችሁት የመልዕክታችን ይዘትና ÷ ዓላማ ወንጌላዊ ነው:: ይህንንም የምናከናውነው በሁለት አቅጣጫ ነው:: ይኸውም በአንድ በኩል÷አማኞችን በቃሉ ማጽናናትና ማበረታታት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በደጅ ያሉትን ወደ ጌታና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመጋበዝ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ያስተማረንን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማርን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ነው:: ጌታም ከእኛ ጋር ነው::

በዚህ መልዕክት የአብያተ ክርስቲያንን እረኞችና ሽማግሌዎች የምንጠይቀው፡- ይህንን ደብዳቤ በምታነቡበት ጊዜ ሁሉ የጌታ መንፈስ በሚያሳስባችሁ በኩል እንድትተባበሩን ነው:: ከሁሉ ይልቅ ይህ የምናደርገው ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ለጌታ ፍሬ እንዲያስገኝ የቅዱሳን ፀሎት ያስፈልገናል:: በተጨማሪም ይህንን ቋንቋ ለሚያነቡ ብዙ ሰዎች መድረስ እንድንችል በአካባቢያችሁ በሰፊው ለማሰራጨት እንድትረዱን እንጠይቃለን:: አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ደብዳቤአችንን አባዝተው ለፈቃደኛ አንባቢ ማሰራጨት ቢወዱ ከእኛ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም:: (አንዳች ለውጥ ለማድረግ ግን ፈቃድ ያስፈልጋል) ጠቃሚ ምክሮችን ለግሱን :: ጌታ ይባርካችሁ::

# የቴፕ መልዕክት

ባለፈው ወር ደብዳቤአችን የቴፕ መልዕቶች ዝርዝር መግለጻችን ይታወሳል:: በወቅቱም ቴፖቹን አዘጋጅቶ ለአድማጮች ማድረስ የሚፈጀውን ወጪ ተምነን እንደምናሳውቅ ገልጸን ነበር:: እርሱም እንደሚከተለው ነው::

**ውዱ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ና!** $8.00
( ከቤኒ ሂን ) ( ጥራት ባለው አልቦም የተጠረዙ ሁለት ቴፖች )

| | |
|---|---|
| የድል ደረጃዎች | ከዮንጊ ቾ |
| ራስን በክርስቶስ ውስጥ ማየት | " |
| የማሰብና የመጠየቅ ሕግ | " |
| አዲስ ፍጥረት | ከዮንጊ ቾ |
| መንፈስ ቅዱስ | " |
| ደኅንነትና ጉስቁልና | " |
| የእግዚአብሔር አድራሻ | " |
| ድል በክፉ ኃይላት ላይ | " |

. እያንዳንዱ $4.00 (መላክያ ዋጋ ያጠቃልላል)

---

**ስለ ቴፖቹ÷** Money Order ወይም ቼክ ስትልኩ ፡- Melaku Tizazu በሚል ስም እንድትልኩ በትሕትና እንጠይቃችኋለን::